# መንፈሰ  አባማ




























ከአፍሪካዊት ጥቁር አምባ - ከሰው ዘር ግንድ ፍጥረተ-ዓለም፣
ከኖረባት የዕትብቱ አፈር - በነጻነት፣ ፍቅር፣.. ሰላም፣
በጭካኔ ተፈንግሎ - በሠንሰለት ተጠፍሮ፣
እናት ከልጅ፣ አባት ከልጅ. . . ከቤተሰብ ተሰውሮ፣
በዕርዛት፣ በቸነፈር፣ . . . በራብ-ጠኔ ተገዝግዞ፣
በእርኩስ መርከብ ታጭቆ - ለ«አዲስ ዓለም» ስቃይ ጉዞ፤

...ያለሥሙ ሥም ወጥቶለት - «ስሌቭ» ባሪያ ተሰኝቶ፣
ለሰው ልጅ ዘር እንደ እንሰሳ - ዋጋ ተመን ተገምቶ፣
ባደባባይ በጨረታ - ካንዱ ባንዱ ተሸምቶ፣
ለአገዳ፣ ለትንባሆ ... - የርሻ ማሳ ተሰውቶ፣
በሰቆቃው ሕይወት ዓለም - ላብ ገብሮ ደሙን ተፍቶ፣
አፍሪቃዊው «ጥቁር መንፈስ» - ባሜሪካ ኖረ ዋቶ፤

...አርባ ጅራፍ ቢገረፍም - ባንገት ገመድ ቢንጠለጠል፣
እንደ ዶሮ ብልት ሥጋ - ቋንጃው ከእግሩ ቢገነጠል፣
በእግረ-ሙቅ ቢጠፈርም - በማረሻ ቢተኮስም፣
እንደ ቁስ የቤት ዕቃ - እንደ ንብረት ቢቆጠርም፣
እንደ ውሃ ጠብታ - ቀስ.. በቀስ.. ድንጋይ ሰብሮ፣
አፍሪቃዊው ጥቁር መንፈስ - በላይ ዋለ ክብሩ ገኖ!

በዘመናት ትግል ፍልሚያ - ከባርነት ለነጻነት፣
ከትውልድ ወደ ትውልድ - ተሸጋግሮ በአብነት፣
«ብላክ ሬቢሊዮን» በ ፓል ቦግል ... መሪ ፋና፣
ያሠረጸው ትግል መንፈስ - የእሳት ሰደድ ባለዝና፣
በየወቅቱ ታጋይ ወልዶ - ለ«ይቻላል» መንገድ መርቶ፣
.. በፍሬድሪክ ዳግላስ ልብ ውስጥ - በደም ሥሩ ሰርጎ ገብቶ፣
«አርንት አይ ኤ ውመን?» - የሰውነት መጠይቅ በሰርነር ትሩዝ አስነስቶ፣
በጃዝ ሪትም በሙዚቃ - ብሶት ጥሪውን አስተጋብቶ፣
በአድዋ ተመስሎ - ነጻነትን ላለም ዘርቶ..፣
ቡክርቲ ዋሽንግተን .. ማርቆስ ጋርቬይ .. በ ዱ. ቦይስ...
በ«አውቶቡስ ወንበር» ሰበብ - በእመቤት ሮዛ ፓርክስ...፣
ለሰውነት መብት ክብር - የዘለቀ ጥቁር መንፈስ...፤
በማርቲን ሉተር ቁጭት ፈጥሮ፣
በነጻነት አደባባይ - ሚሊዮኖች አስቆጥሮ፣
«አይ ሃቭ ኤ ድሪም..» ሕያው ቃሉ፣
የእኩልነት ራዕይ ውሉ፣
ጊዜ ትውልድ አስገብሮ- ሰንሰለቱን ሰባብሮ፣
ምርጫ መብቱን አስከብሮ - እኩልነት አስነግሮ፣
ጊዜው አክትሞ - የጣር ሥቃይ የሰቆቃ፣
በዘመናት መስዋዕትነት - ያለም ቁንጮ ሊሆን በቃ!!

በድል ቆመ ባለም ማማ
የፍቅር መንፈስ፣ የፍትህ መንፈስ.. . በኦባማ!
የለውጥ ቤዛ ሐዋርያ «ይቻላል»ን ያስከበረ፣
ነጭ፣ ጥቁር፣ ቢጫ፣ ጠይም... - በሰው ዘር ልብ ውስጥ ያደረ፣
የነጻነት፣ የእኩልነት... ፍትህ ዓርማው ፍቅር ሰላም፣
ኦባማዊ ሕያው መንፈስ - ይኑርልን ለዘልዓለም!!

ጌታቸው አበራ
፳፻፩ ዓ/ም
(ኑቬምበር 4/ 2008)




















